EthioLion

EthioLion.Com

## በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ጽ/ቤት በፍርድ ቤት ውሳኔ ስሙንና ዓርማውን አስከበረ።

በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ጽህፈት ቤት ከአራት ዓመት በፊት በካናዳ መንግሥት በሕጋዊ መንገድ ስሙንና ዓርማውን አስመዝግቦ ሲንቀሳቀስ የነበረውን የቅንጅት የድጋፍ ድርጅትን ለማዳከምና ለማጥፋት ከ 2 ዓመት በፊት የቅንጅትን ስምና ዓርማ ያለአግባብ በመጠቀም በድጋፍ ድርጅቱ ላይ ችግር በመፍጠርና ደጋፊውን ግራ በማጋባት ላይ የነበሩትን በሕግ ፊት ማቅረቡ ይታወሳል።

ባለፈው ኤፕሪል 22 ቀን 2009 (ሚያዝያ 2001 ዓ.ም) የኦንቶሪዮ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያለአግባብ ስሙንና ዓርማውን ሲጠቀሙ የነበሩትን ግለሰቦች በማንኛውም መንገድ በየትኛውም ዓይነት ሁኔታና ቦታ የቅንጅትን ስምና ዓርማ እንዳይጠቀሙ የሚል የእቀባ ውሳኔ በመስጠቱ ውሳኔው ወዲያውኑ ተፈጻሚ ሆናል። በዚህም መሰረት ተከሳሾቹ ሰቅለውት የነበረውን የቅንጅትን ስምና አርማ እንዲሁም በድህረ ገፃቸው ላይ የነበረውን ማንሳታቸው ተረጋግጧል።

ካናዳ የሕግ የበላይነት ያለበት አገር በመሆኑ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ አካል የሆነው የቅንጅት የባሕልና የእርዳታ ድርጅት ጽህፈት ቤት መብቱን ለማስከበር በቆራጥነት ያደረገው ትግል ውጤት በማግኘቱ አባላትና ደጋፊዎች የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል።

## "የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ቀን" 4ኛ ዓመት መታሰቢያ በቶሮንቶ፣ ካናዳ በሕዝባዊ ስብሰባ እንደሚከበር ተገለፀ።

የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ድርጅት በካናዳ የሚያደርገውን ትግል በተጠናከረ ሁኔታ ለመቀጠል በአዲስ መንፈስ በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጹን ያሰማበትን የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ፡ም በማሰብ ላለፉት ሶስት ዓመታት "የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ቀን" በሚል ሲያከብር መቆየቱ ይታወሳል። በዚህም መሰረት ዘንድሮም ለአራተኛ ጊዜ እሑድ ሜይ 17 ቀን 2009 (ግንቦት 9 ቀን 2001 ዓ.ም) ለማሰብ 427 Bloor St. West በሚገኘው አዳራሽ ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 2:30 p.m. ጀምሮ በሕዝባዊ ስብሰባ ለማክበር በመዘጋጀት ላይ ይገኛል። በዚህም "የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ቀን" በዓል ላይ ስለመጪው ትግል ደጋፊው ክፍል ማድረግ የሚገባውን በማንሳት ውይይት የሚደረግና በምርጫ 97 ወቅት በውጭ ደጋፊው ዘንድ የነበረውን የሕዝብ ስሜትና ድጋፍ ለማምጣት ጽህፈት ቤቱ ቆርጦ መነሳቱን ያስታወቃል።

የቅንጅት መኢአድ ድጋፍ ጽህፈት ቤት
ቶሮንቶ፣ ካናዳ

Ethiopia will prevail !